# ሻሽ አህመድና ወንድሞቻቸው



38 ቤተሰቦች በመሆን የመርካቶን አደሬ ሠፈር የመሠረቱት ሐረሪዎች ከአዲስ አበባ ከተማ የንግድ ታሪክ ጋር በተያዘ ሊነገርላቸው የሚችል ብዙ ነገር አለ። አንዱ በቤተሰብ ደረጃ ተባብረው የመሥራት ባህላቸው ነው። ሠርተው ባፈሩት ሀብት ትላልቅ የግንባታ ሥራዎችን በማከናወንም ለአዲስ አበባ በተለይ ለመርካቶ ዕድገት ቀላል የማይባል አስተዋጽኦ አድርገዋል። እርስ በእርስ መረዳዳታቸውም ሌላው መለያቸው ነው።

ከሐረር መጥተው በመርካቶ ውስጥ ትላልቅ የግንባታ ሥራዎችን ማከናወን ከቻሉት ሐረሪዎች መሐል ሐጂ ኢብራሂም መሐመድ ሸኖ ፣ ሐጂ ሙክታር ሱከር ፣ አቶ አብዱላሂ አህመድ፣ አቶ ካሳዬ ተሾመ ፣ሐጂ አብዱልሠመድ ኢብራሂምና ቤተሰቦቻቸውን መጥቀስ ይቻላል። ከእርመኖች በመቀጠል ለአፄ ኃይለሥላሴ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ልብስ ሰፊ መሆን የቻሉት ሐጂ ሻሽ ቀሉም ከሐረር መጥተው ታላቅ ባለሙያ መሆን ችለዋል።

ሐጂ ሻሽ አህመድና ሁለቱ ወንድሞቻቸውም መርካቶ ውስጥ የሚታይ ነገር አኑረው ያለፉ የሐረር ተወላጆች ነበሩ። ከሶስቱ ወንድማማቾች በመጀመሪያ ወደ አዲስ አበባ የመጡት ታላቅየው ሐጂ ሻሽ ሲሆኑ ዘመኑ እ.ኤ.አ 1920 ነበር። በመቀጠል ሁለቱ ወንድሞቻቸው ሐጂ ሙሜና ሐጂ አቡበከር ወደዚህ መጡ።

በ1912 ዓ.ም አካባቢ ወደ አዲስ አበባ የመጡት ሐጂ ሻሽ ሥራ የጀመሩት ጊዮርጊስ አካባቢ ይገኝ በነበረው አራዳ ገበያ በሕንዳዊያን ጨርቃ ጨርቅ ሱቅ ተቀጥረው በማገልገል ነበር። የቁርዓን ትምህርትና በአረቢኛ ቋንቋ እውቀቱ የነበራቸው ሶስቱ ወንድማማቾች በዚህ መልኩ ከሐረር ወደ አዲስ አበባ መጥተው

በመሥራት የራሳቸውን ካፒታል ማፍራት ከቻሉ በኋላ ሥራ በጀመሩበት አራዳ ገበያ በጋራ የጨርቃ ጨርቅ ሱቅ ከፈቱ።

ፋሽስቱ ጣሊያን የአረዳ ገበያን ወደ መርካቶ ሲመራው ሶስቱ ወንድማማቾች አንድ የድንጋይ ሱቅ በጋራ ሠርተው የንግድ ሥራቸውን ማከናወን ቀጠሉ ። ጠላት ከተባረረ በኋላ ታላቅየው ሐጂ ሻሽ አህመድ ፒያሳ ላይ የተዘጋጁ ልብሶች መሸጫ ሱቅ ከፈቱ። በዚያን ወቅት በፒያሳ ዙሪያ በዚህ የንግድ ዘርፍ የተሰማሩ ብቸኛው ኢትዮጵያዊ ስለነበሩ ብዙ የመኳንንትና መሳፍንት ቤተሰቦችን በደንበኝነት መያዝ ችለው ነበር።

በዚያ አጋጣሚ ባፈሩት እውቂያ ምክንያት ከአልጋ ወራሹ ጋር መቀራረብ በመቻላቸው ፤ ብዙ ከለፉበት በኋላ አልተሳካም እንጂ፤ በደሴ ከተማ የዘይት ፋብሪካ በጋራ የማቋቋም ዓላማ ነበራቸው። በቤተመንግስቱ በፕሮቶኮል ደረጃ ከሚጋበዙት የዘመኑ ሰዎች አንዱ ነበሩ ። በዚያን ወቅት ሳምንቱን ሙሉ በቁርስ በምሳና በራት ሰዓት ወደ ቤተ መንግስት ከሚጠሩት ባለስልጣናትና ታዋቂ ግለሰቦች አንዱ ሆነው የተመረጡት ሐጂ ሻሽ በሳምንት ሐሙስ የምሳ ሰዓት ተጋባዥ ነበሩ።

ከሶስቱ ወንድማማቾች በንግዱ ሥራና በነበራቸው ልዩ ትጋት ሐጂ ሻሽ የተለየ ዕውቅና ነበራቸው ። በዘመኑ በልዩ ሞዴልነቱ የሚታወቅና ስሪቱ አሜሪካ የሆነ ‹‹ ናሽ›› መኪናም ነበራቸው ። በዚህም የተነሳ ‹‹ ሐጂ ሻሽ ባለ ናሽ›› ተብለው እስከመጠራት ደርሰዋል።

የወንድማማቹ የሽርክና ሥራ በተለየ ሁኔታ የተገለፀው የራስ ኃይሉ ሲኒማ ቤት ( ሲኒማ ራስ) አጠገብ መሬት በጋራ ገዝተው አንድ ብሎክ የድንጋይ ቤት በገነቡበት ወቅት ነበር። ከ 1952 -1961 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ የነበሩት ዘውዴ ገ/ሕይወት አዲስ አበባን ለማልማት ተንቀሳቅሰው አሮጌ ቤቶችን እያስፈረሱ አዳዲስ መንገድና ሕንፃዎች እንዲሰራ ሲያደርጉ ሐጂ ሻሽና ሁለቱ ወንድሞቻቸውም የድንጋይ ሱቆቻቸውን አፍርሰው ባለ ሶስት ፎቅ ሕንፃ ገነቡ። አሁን ሲኒማ ራስ አጠገብ የሚገኘው የሐረር ሆቴል ሕንፃን የሰሩት ሶስቱ ወንድማማቾች በጋራ ነበር።

በመጠነ ሰፊ የበጎ አድራጎት ሥራቸው ይታወቁ የነበሩት እነዚህ ቤተሰቦች የመርካቶው አንዋር መስጊድ አገልግሎት መስጠት ሲጀምር መብራት ስላልነበረው

ለመጀመሪያ ጊዜ ለመስጊዱ የመብራት ቆጣሪ ያስገቡትና ለብዙ ዓመታትም መብራቱ የቆጠረውን ሂሳብ ይከፍሉ የነበሩት ወንድማማቾች ነበሩ።

አሁን በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ሰባት ያህል ቅርንጫፎች ያሉትና ሐረርን በመሠረቷት ሺህ አባድር ሥም የሚጠሩትና በሐረሪ ማህበረሰብ አባላት በ1954 ዓ.ም ለተመሠረተው ትምህርት ቤትም የሶስቱ ወንድማማቾች አስተዋጽኦ ቀላል የሚባል አልነበረም ። መገኛ አድራሻው የመርካቶው ፔፕሲ ኮላ ፋብሪካ ያለበት አካባቢ የነበረውና ‹‹ ሠለፊያ›› በሚል የሚጠራው ፤ ለአዲስ አበባ ከተማም የመጀመሪያው የሙስሊም ትምህርት ቤትንም በመመሥረትና ሥራው እንዲቀጥል ሶስቱ ወንድማማቾች የድርሻቸውን ለግሰዋል።

ባለትዳርና በርካታ ልጆችን አፍርተው ያለፉት ሐጂ ሻሽና ወንድሞቻቸው ወላጆቻቸውን ከሐረር ወደ አዲስ አበባ አስመጥተው ይጦሩ ነበር።

